**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ**

**በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት**

**(Asset Recovery Directorate)**

በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት ፍትህ ቢሮው የስራ ክፍሎችን በ2015 ዓ.ም መጀመሪያ እንደገና አደረጃጃት ሲሰራ በአዲስ ከፍቶ ወደ ስራ ያስገባው የስራ ክፍል ነው፡፡ የስራ ክፍሉም በዋናነት በወንጀል የተገኘ ንብረት ማስመለስ በሚቻልባቸው በሙስና ወንጀል ህጎች (አዋጅ ቁጥር 434/97 በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለው እና ሌሎችም)፣ በወንጀል የተገኘ ሀብት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኛን በገንዘብ መርዳት ህግ (አዋጅ ቁጥር 780/2005)፣ በሰው የመነገድ እና በህገ ወጥ መንገድ ሰዎችን ድንበር የማሻገር ህግ (አዋጅ ቁጥር 1178/2012)፣ የወንጀል ህግ እና በመሳሰሉ የንብረት ውርስ በሚያስከትሉ የሀገሪቱ ህጎች በጠቅላላው ለዐቃቤ ህግ የተሰጠውን ስልጣን እንዲሁም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት በማድረግ እየሰራ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በክልሉ **ከወንጀል ጋር የተገናኙ ንብረቶችን ከማንኛውም ቦታና ሰው ለማስመለስ የሀብት ምርመራና የማስመለስ ስራዎችን ለማከናወን** በወንጀል የተገኘን ንብረት በባለቤትነት ለማስመለስ ፍትህ ቢሮ ሃላፊነቱን ወስዶ በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት በቢሮ ውስጥ አደራጅቶና የአሰራር ማኑዋል አዘጋጅቶ ወደ ስራ አስገብቷል፡፡ ስለሆነም ከላይ ከተጠቀሱት ህጎች እና የአሰራር ማኑዋሉ መረዳት እንደሚቻለው የስራ ክፍሉ የሚከተሉት ተግባርና ላፊነት ይኖሩታል፡-

1.1. ከማንኛውም አካል የሚቀርቡ ጥቆማዎችን መነሻ በማድረግ የሀብት ምርመራ ሥራ ማከናወን፤
1.2. ጥቆማዎችንና ጠቋሚዎችን ይመዘግባል፣ በሚስጥር ይይዛል፣ ሕግ በሚፈቅደው መሰረት ተገቢውን ጥበቃ መደረጉን ማረጋጥ፤
1.3. በወንጀል ተግባር የተገኙ የወንጀል ፍሬዎች፣ የወንጀል ድርጊት ለመፈጸም ጥቅም ላይ የዋሉ ንብረቶች፣ ከወንጀል ከተገኘ ሀብት ጋር የተቀላቀሉ ንብረቶች እንዲሁም በወንጀል የተገኙ ንብረቶችን በመጠቀም የተፈራ ሀብት ማጥናት/መመርመር፤
1.4. የንብረት ግምት በሥራ ክፍሉ ወይም በሌሎች ባለሙያዎች ማሰራት/እንዲሰራ ማስደረግ፣

1.5. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት የያዙ ግለሰቦች፣ የመንግስት ባለስልጣናትና ሠራተኞች፣ የአገር ዉስጥና የዉጭ አገር ኩባንያዎች፣ ከኩባንያዎቹ በስተጀርባ የሚገኙ የመጨረሻ ተጠቃሚዎች ወይም ባለቤቶች (Beneficiarry Owners)፣ የእነርሱን ቤተሰቦች፣ ዘመዶች፣ የንግድ ሽሪከችና ማንኛዉም በወንጀሉ የተሳተፉ ሰዎችን በምርመራ መለየት፤

1.6. በወንጀል ተግባር የተገኘ እና ከአገር ዉጭ የሸሸን ሀብት ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር በትብብር በመስራት ለማስመለስ ጥያቄዎችን ማቅረብ እንዲሁም በህግ አግባብ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ የሕግ ትብብር (Formal & Informal Legal Assistance) ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃና ማስረጃ ማሰባሰብ እንዲቻል እገዛ ማድረግ፤

1.7. ሕግ በሚፈቅደዉ አግባብ በወንጀል የተገኘ ሀብት ለመለየት የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን ከማንኛዉም አካል ማሰባሰብ፤

1.8. ሕግ በሚፈቅደዉ አግባብ ልዩ የምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም በወንጀል የተገኘ ሀብትንና የወንጀል ፈጻሚዎች ለመለየት የሚያስችሉ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ፤

1.9. ሀብቱ በወንጀል ተግባር የተገኘ ስለመሆኑ ለመጠርጠር በቂ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ በሕግ አግባብ ዕግድ በማውጣት በህገ ወጥ መንገድ የተገኙ ወይም ተያያዥ ንብረቶችን ማሳገድ፣ የታገዱ እና የተያዙ ንብረቶች ላይ አስተዳዳሪ ማሾም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አስተዳዳሪ እንዲሾም ለፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ፣ ንብረቶች በአግባቡ መያዛቸዉን ይከታተላል፣ የንብረቶቹ አስተዳደር ከብክነት በጸዳ መልኩ በህግና በተዘረጋው አሰራር መሰረት መከናወኑን ይከታተላል፣ የተጓደለ ነገር ሲኖር የማስታካከያ እርምጅ ይወስዳል ወይም እንዲወሰዱ ያደርጋል፣ ብክነት ሲኖር ወይም ኃላፊነትን ባለመወጣት የደረሰ ጉዳት ሲኖር ድርጊቱን በፈጸሙ አካላት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል ወይም መወሰዱን ያረጋግጣል፣

1.10. የመንግስት ባለስልጣናትና ሠራተኞች እንዲሁም ከእነዚህ ጋር የጥቅም ትስስር ያላቸዉ ሰዎች በወንጀል ተግባር ከገቢ በላይ ያፈሩትን ሀብት ወይም ምንጩ ያልታወቀ ንብረት የመመርመር እና በሕግ አግባብ ማስመለስ፣

1.11. በወንጀል የተገኘ ሀብትን የወንጀል ፍርድን (Conviction Based) ወይም /እና የወንጀል ፍርድ ሳይኖር (Non-Convection Based) ሀብት የማስመለስ ስርዓቶችን

ተጠቅሞ በህገ ወጥ መንገድ የተገኙ ንብረቶችን ለማስመለስ የሚያስችል ክስ ከወንጀል ክስ ጋር በተጓዳኝ ወይም በተናጠል በማቅረብና በመከራከር የሕዝብና የመንግስት ሀብት የማስመለስ ሥራ ያናከዉናል፣ እንዲሁም በፍትሐብሔር የክስ ሂደት እንደሚመለስ ያስደርጋል፤

1.12. በወንጀል የተገኘውን ንብረት ማስመለስ ጋር በተያያዘ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ድርድር ያደርጋል ፤ የድርድር ዉጤቱ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

1.13. በህግ መሰረት የተወረሱ ንብረቶች ሥልጣን ላለው መንግስት አካል ገቢ መደረጉን ወይም ለሚመለከተው ተመላሽ ስለመሆኑ ያረጋግጣል ፤

## ለግንዛቤ ማስጨበጫ

## 2. በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ በአማራ ክልል

### 1. መግቢያ

- ወንጀል በተለያየ አላማ ሊፈጸም የሚችል ቢሆንም ገንዘብ የሚያስገኙ ኢኮኖሚ ነክ ወንጀሎች የሚፈጸሙት ግን በዋናነት ከወንጀል ድርጊታቸው የገንዘብ ትርፍ ለማግኘት ስለመሆኑ ብዙ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በመሆኑም በሰው የመነገድና በህገ ወጥ መንገድ ሰዎችን ድንበር የማሻገር፣ የሙስና ወንጀሎች፣ የተከለከሉ ዕፆችን ማዘዋወር፣ የሃሰት ገንዘብ ማተም፣ ኮንትሮባንድ፣ የጦር መሳሪያ ማዘዋወር እና ንግድ፣ እገታ፣ ውንብድና፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት፣ የሽብር ወንጀሎች እና የመሳሰሉት ወንጀሎች የሚፈጸሙት የገንዘብ ጥቅም ለማግኘት ታሳቢ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

- አንድ የወንጀል ድርጊትን ተከትሎ ወንጀለኞች ላይ የተለያዩ አላማዎችን የያዙ ቅጣቶች እና ትዕዛዞች በፍርድ ቤት ይተላለፋሉ፡፡ በተለመደው የወንጀል መከላከል ሂደት ውስጥ አንድ ሰው ወንጀል ፈጽሞ ከተገኘ እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል ወይም በፅኑ እስራት፣ በሞት ወይም በገንዘብ በመቅጣት ወንጀልን የመከላከል ሂደቱ ብዙ እርቀት ተጉዟል፡፡ ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከወንጀል ድርጊቱ የሚገኘው የገንዘብ ትርፍ ከፍተኛ እየሆነ በሄደ ቁጥር ወንጀል ፈጻሚዎች ከድርጊታቸው የገንዘብ ትርፍ እስካገኙ ድረስ መታሰርና በገንዘብ መቀጣትን የተለመደና የማያስተምራቸው እየሆነ መጥቷል፡፡

- ስለሆነም ዓለም ላይ ያሉ ሀገሮች የገንዘብ ጥቅም የሚያስገኙ የኢኮኖሚ ወንጀሎች በመፈፀም በወንጀለኞች የተወሰዱ ንብረቶችን ለማስመለስ እና የወንጀል ፍሬውን ወንጀለኞች እንዳይጠቀሙበት ለመከላከል በማሰብ በወንጀል ድርጊት ያገኙትን ንብረት መዉረስን እንደ አንድ ጥሩ ዘዴ ይጠቀማሉ፡፡

- ውርስ ማለት የንብረት ባለቤትነትን በፍርድ ቤት ወይም ሌላ ስልጣን ባለው አካል በቋሚነት ማሳጣት ማለት ነው፡፡

- በወንጀል የተገኘ ንብረት ማስመለስ ማለት ደግሞ በህግ መሰረት ውርስ በሚፈፀምባቸው ከሁሉም የወንጀል ድርጊቶች በህገ ወጥ የተገኘን ገቢ ወይም ትርፍ የማስመለስ እና ለንብረቱ ባለቤት የመመለስ አጠቃላይ ሂደቱን የሚመለከት ነው፡፡

- የመውረስ ህግ ከጊዜ ጊዜ እድገት እያሳየ ከመሄዱም በተጨማሪ አስተማሪነቱና ወንጀልን በመከላከል ረገድ ያለው ሚና በገንዘብ ከመቅጣትና ከማሰር የተሻለ እንደሆነ እና ተፈፃሚ መሆን እንዳለበት ዓለም አቀፍ ሰነዶች ምክረ ሀሳባቸውን ይለግሳሉ በተመሳሳይ የተለያዩ ጥናቶችም ያሳያሉ፡፡

- በኢትዮጵያም ይህንን አይነት በወንጀል የተገኘን ንብረት የማስመለስ ሂደት የሚከናወንበት በተበታተነ መንገድ በተለያዩ የሀገሪቱ አዋጆችና በወንጀል ህጉ ውስጥ ተካቶ እናገኘዋለን፡፡

## 2. <u>በወንጀል የተገኘ ንብረት ማስመለስ ዓላማ እና ጠቀሜታ</u>

### 2.1. <u>ዓላማ</u>

- ወንጀለኞች በወንጀል ድርጊታቸው ያገኙትን የገንዘብ ወይም የንብረት ጥቅም እንዳይጠቀሙበት ማድረግ፤

- ወንጀለኞች በወንጀል ያፈሩትን ንብረት የበለጠ ወንጀል ለመፈፀም መሳሪያ እንዳያደርጉት፣ የተደራጁ ወንጀለኞች እንዳይፈጠሩ ወይም ሽብርተኝነትን መርዳትን ለመካለከል፤

- ወንጀለኞች በወንጀሉ ምክንያት ያገኙትን ንብረት ወይም ያደረሱትን ጉዳት የንብረቱ ባለቤት ለሆነው ወይም ጉዳት ለደረሰበት ህዝብና መንግስት እንዲመለስ ማድረግ፤

### 2.2. ጠቀሜታ

- የተመዘበረው ንብረት እንዲመለስ ተደርጎ በአግባቡ ለልማት እንዲውል ያግዛል፣
- ከወንጀለኛው ንብረቱ እንዲመለስ መደረጉ ቀጣይ ወንጀል እንዳይፈፅም ያደርጋል (prevention)፣
- የተመዘበረው ንብረት መመለሱ ወንጀለኛው እንዲማርበት እና ሌሎች እንዲጠነቀቁ ያደርጋል (deterrence)፣
- በአጠቃላይም የንብረት ማስመለስ ጥንካሬ የወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ጥንካሬ እንደማሳያ ይሆናል፤ ህብረተሰቡም በፍትህ ስርዓቱ ላይ ያለውን አመኔታ ያሳድጋል፡፡

## 3. በወንጀል የተገኘ ንብረት በማስመለስ ሂደት ውስጥ የሚሰሩ ዋና ዋና ስራዎች

በወንጀል ምክንያት የሚመዘበርን ንብረት ለማስመለስ በማስመለስ ሂደቱ ውስጥ በርካታ ስራዎች የሚከናወኑ ቢሆንም በዋናነት ግን የሚከተሉትን ተግባራት መያዝ ይቻላል፡፡

- **መለየት**፡- ለሀብት ጥቆማው መነሻ የመረጃ ምንጮችን፣ የሚሰበሰበውን ማስረጃ፣ ሃላፊነት ያለባቸውን ሰዎች ወይም የሚመለከታቸውን ቡድኖች፣ ተፈፃሚ የሚሆኑ ህጎችን፣ ለስራው አጋዥ የሆኑ ተቋማት እና የመሳሰሉት ለሀብት ማስመለስ እንዲረዳ አስቀድሞ የመለየት ስራ መስራት ተገቢ ነው፣
- **ጥናት**፡- ንብረት የሚጠናው ወደፊት የወንጀል መዝገቡ በፍርድ ሲጠናቀቅ ለንብረት ውርስ የሚሆን በቂ ንብረት ለማቆየት ነው፡፡ የተመዘበረውን ንብረት በመከተል ወይም ምንጩ ያልታወቀውን ንብረት ለመለየት የሚጠናበት ነው፡፡ ስለሆነም የተጠርጣሪን/ተያያዥ ሰዎችን ንብረት ማጥናት/መመርመር፣ ንብረቱን ከወንጀሉ ጋር ማገናኘት የመሳሰሉ ስራዎችን ራሱን አስችሎ መመርመር የሚያስፈልግ ነው፣ በተቻለ መጠን የሀብት ጥናት ወይም ምርመራ ከወንጀል ምርመራው ጋር ጎን ለጎን መከናወን ይኖርበታል፤
- **ዕግድ**፡- ንብረት ማሳገድ፣ በንብረት ጥናት ወቅት በተጠርጣሪው ወይም በቅርብ ዘመዶቹ ስም የተመዘገበ ንብረት ከተገኘ ይህ ንብረት እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ

ወይም በማንኛውም መንገድ ወደ ሶስተኛ ወገኖች እንዳይተላለፍ ለማድረግ በፍርድ ቤት እንዲታገድ ማድረግ ነው፡፡ በንብረት ጥናት የተገኙ የወንጀል ፍሬ እና የወንጀል መፈጸሚያ የሆኑ ንብረቶች እንዳይሸሹ፣ እንዳይንቀሳቀሱ፣ ወይም ለብልሽትና ለጉዳት እንዳይጋለጡ መከበር አለባቸው ፣ የዕግድ ትዕዛዝ በፍርድ ቤት የሚሰጥ አሰገዳጅ ትዕዛዝ ሲሆን የግዴታ ንብረቱ ተይዞ መቆየት ላይጠይቅ ይችላል፤

- ***መያዝ***፡- እንደ ሁኔታው ንብረትን መያዝ፣ ንብረት የሚያዘው የውርስ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ንብረቱን ከመጥፋት፣ ከመበላሸትና ለሌላ ወገን ከመተላለፍ ለመጠበቅና ተጠርጣሪው በወንጀሉ ባገኘው ንብረት እንዳይጠቀም ለመከላከል የሚሰራ ተግባር ነው፤
- ***ንብረት አስተዳደር***፡- ንብረት ማስተዳዳር፣ ወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ ንብረት ከታገደ ወይም ከተያዘ በኃላ የታገደው ንብረት ባህሪ ንብረት ጠባቂ እንዲሾምለት የግድ የሚል ከሆነ ገለልተኛ የሆነ እና እንደ ንብረቱ አይነት የተለየ ዕውቀት ያለው ንብረት ጠባቂ እንዲሾም ይደረጋል፡፡ የታገደውን ንብረት ዋጋ እና ደህንነት ጠብቆ ለማቆየት ይጠቅማል፤
- ***መውረስ***፡- የውርስ አቤቱታ በማቅረብ ንብረቱ እንዲወረስ ማድረግ፤ መውረስ ተከሳሽ በንብረት ላይ ያለውን መብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚያጣበት ስርዓት ነው (change of ownership from the accused to the state) እና
- ***መረከብ/ማስፈፀም***፡- በወንጀሉ ምክንያት የተወሰደውን ንብረት ወይም ተመጣጣኝ ማካካሻ ንብረቱን ለንብረቱ ባለቤት ወይም ጉዳት ለደረሰበት አካል እንዲመልስ /እንዲረከብ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡

## 4. የውርስ አይነቶች

ከሚወረሰው የንብረት አይነት አንጻር የውርስ አይነቶች በ 3 ዋና ዋና ክፍሎች ሊከፈል ይችላል፡፡ እነሱም፣

1. ***የወንጀል ፍሬን መውረስ*** (Object Confiscation) ይህ የመውረስ አይነት ወንጀል ፈጻሚው ከፈጸመው ወንጀል በቀጥታ ያገኘውን ገንዘብ/ንብረት እንደሚወረስበት

የሚያመለክት የመውረስ አይነት ነው፤ በቀጥታ የተገኘው የወንጀል ፍሬ በመጠቀም የተገኘ ሌላ ገቢ/ትርፍ፣ ተቀላቅሎ ወይም ተለውጦ የተገኘ ፍሬ በዚሁ የመውረስ አይነት ውስጥ የሚካተት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

2. **የወንጀል ፍሬን ተመጣጣኝ መጠን መውረስ** (Value Confiscation) ወንጀል ፈጻሚው ወንጀል ፈጽሞ ያገኘውን ቀጥተኛ ገንዘብ/ንብረት ማግኘት ባልተቻለ ጊዜ ወይም በወንጀሉ ለደረሰ ጉዳት ማካካሻ ከወንጀሉ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን ተመጣጣኝ የሆነ የወንጀል ፈጻሚውን ንብረት እንዲወረስ የሚደረግበት የመውረስ አይነት ነው፡፡ ይህ የመውረስ አይነት ከወንጀሉ ያገኙትን የወንጀል ፍሬ በተለያየ መልኩ በማሸሽ ወይም እንዳይገኝ በማድረግ የህጉን አላማ ለማሳካት ያልተቻለ በሆነ ጊዜ ያገኙትን ጥቅም ተመጣጣኝ ንብረት እንዲወረስ በማድረግ ማንኛውም ሰው ከወንጀል ድርጊቱ ጥቅም እንዳያገኝ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ያለው የመውረስ ሂደት ነው፡፡

3.**ለወንጀል መፈጸሚያ የዋለ ንብረትን መውረስ** (Instrumentality confiscation) ወንጀሉን በመፈጸም ሂደት ውስጥ ወንጀሉን ለመፈፀም የተጠቀመበትን ንብረት ወይም እንደ ወንጀሉ ባህሪ ወንጀሉን ለመፈፀም የተዘጋጀባቸው እና የተሰናዳባቸው ንብረቶች እንዲወረስ የሚወሰንበት የመውረስ አይነት ነው፡፡

## 5. የመውረሻ መንገዶች

1. **በጥፋተኝነት ላይ የተመሰረተ ውርስ** (Conviction Based Confiscation or Criminal Confiscation) የወንጀል የጥፋተኝነት ውሳኔን መሰረት አድርጎ በተከሳሽ ላይ የሚቀርብ (in personam) የውርስ አይነት ነው፡፡ ወንጀለኛው በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ሲባል እንደአግባብነቱ የንብረት ውርስ አቤቱታው ከወንጀል ክሱ ጋር ወይም ራሱን በቻለ ሁኔታ የወንጀል ጉዳዩን ለያዘው ፍርድ ቤት ሲቀርብ የሚታይበት መንገድ ነው፡፡

2. **በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ ውርስ** (Non-Conviction Based Confiscation or Civil Confiscation or Civil Forfeiture) የጥፋተኝነት ውሳኔ በፍርድ ቤት ማግኘትን የግድ አይልም፤ ዐቃቤ ህግ ድርጊቱ መፈፀሙንና የተያዘው ንብረት የወንጀል ፍሬ (proceed of crime) ወይም ለወንጀል መፈፀሚያ የዋለ (instrumentality of crime) ከወንጀል ድርጊቱ ጋር የተያያዘ መሆኑን በተገቢው የማስረጃ ደረጃ ማስረዳት ሲቻል በወንጀል የተገኘው

ንብረት ውርስ የሚፈፀምበት መንገድ ነው፡፡ የንብረት ውርስ አቤቱታው ህግ በሚፈቅድበት ጉዳይ የወንጀል ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት ቀርቦ የሚታይ ነው፡፡

3. **<u>የፍትሐብሔር ክስ</u>** (Civil Action) በጥፋተኝነት ላይ ከተመሰረተም ሆነ በጥፋተኝነት ላይ ካልተመሰረተ ውርስ የተለየ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ይመራል፤ ተከሳሽ ነፃ በመባሉ፣ ክሱ በመቋረጡ ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ጥፋተኝነት ውሳኔ ካልተገኘ የፍትሐብሔር ክስ በበመስረት በወንጀል የተገኘውን ንብረት መውረስ የሚቻልበት መንገድ ነው፡፡

4. **<u>አስተደዳደራዊ ውርስ</u>** (Adminisrative Confiscation) የፍርድ ቤት ውሳኔ ሳያስፈልግ በሌሎች የአስተዳደር አካላት ውሳኔ ውርስ የሚደረግበት ነው፡፡ በንብረት ላይ የሚቀርብ (in rem action) ነው፣ ተግባራዊ ለማድረግ የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎችና ገደቦች ይኖራሉ፡- ለግለሰቦቹ ማስታወቅ፣ ተቃውሞ አለማቅረባቸው፣ የገንዘቡ መጠንና አይነት የመሳሰሉት ይኖሩታል፡፡

## 6. <u>በኢትዮጵያ በወንጀል ድርጊት የንብረት ውርስን የሚዳስሱ ህጎች</u>

- *በወንጀል የተገኘን ንብረት ህጋዊ አስመልሰሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት* አዋጅ ቁጥር 780/2005፣
- በሰዎች የመነገድና በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር አዋጅ ቁጥር 1178/2012
- የፀረ ሙስና ህጎች ፣
- የወንጀል ህግ፣
- የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ በወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004
- የብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ 591/2000
- የሽብር አዋጅ ቁጥር 1176/2012፣
- የኮምፒዩተር ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 958/2008
- የጦር መሳሪያ አያያዝ እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012

- የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006
- የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009
- የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006
- የንግድ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 980/2008
- የወንጀልና የፍ/ብሔር ስነ ስርዓት ህጎች
- ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው እና ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ የስምምነት ሰነዶች አዋጅ ቁጥር 526/1999፣ 544/1999 እና 545/1999 እና የመሳሰሉት ይገኙበታል

## 7. ተቋማዊ አደረጃጀት

- በወንጀል የተገኘን ሀብት ለማስመለስ ራሱን ችሎ በሀገራችን ሲሰራ የቆየ አይደለም፡፡ የሙስና ወንጀል ጉዳዮችን በሚመለከት ከሙስና ወንጀሎች የስራ ክፍል እንዲሁም በሌሎች ወንጀሎች በተለይ ኢግዚቢት ጋር በተያይዞ አብሮ እንደ ሀገር ሲሰራበት ነበር፤ ነገር ግን ስራው በቂ እና የተፈለገውን ውጤት ያስገኘ አልነበረም፡፡
- በመሆኑም በአዲስ መልክ ለስራው ባለቤት መስጠት የግድ ሆኖ በመገኘቱ በፌዴራል ደረጃ ፍትህ ሚኒስቴር በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት በውስጡ ሶስት የስራ ክፍሎች ማለትም የሀብት ጥናት ምርመራ ማስተባበሪያ፣ የሀብት ማስመለስ ማስተባበሪያ እና የንብረት አስተዳደር ማስተባበሪያ እንዲይዝ ተደርጎ አደረጃጀት በተቋሙ የአደረጃጀት ማኑዋል ተሰርቶለት ወደ ስራ ከገባ ዓመታት አሳልፏል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለም የፌዴራል መንግስቱ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ቁጥር 40(2)-ለ) መሰረት በሀገር ውስጥ እና በሀገር ውጭ የሚገኙ ከወንጀል ጋር የተገናኙ ንብረቶችን እንደሚያስመልስና እንደሚያስተባብር ተግባሩ ለፍትህ ሚኒስቴር ስለመሰጠቱ ተደንግጎ ይገኛል፡፡
- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትም የክልሉን መንግስት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በዝክረ ህግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 280/2014 ቁጥር 28 ንዑስ ቁጥር 8 እና 15(ሀ) መሰረት የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ ስልጣንና ተግባሩ ለፍትህ ቢሮ ተሰጥቶታል፡፡

- ፍትህ ቢሮውም በወንጀል ጉዳይ ላይ በህግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በዚሁ የክልሉ መንግስት የአስፈፃሚ አካላት አዋጅ ቁጥር 280/2014 ቁጥር 11(ሰ) መሰረት በማድረግ ከነሐሴ 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በቢሮው ፀድቆ ተፈፃሚ እየሆነ ባለው የአብክመ ፍትህ ቢሮ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ ማኑዋል ቁጥር 12.1 ላይ እንደተመለከተው የወንጀል ጉዳዮች ዘርፍ በስሩ አራት ዳይሬክቶሬቶችን በመያዝ ተደራጅቷል፡፡
- ከእነዚህም ውስጥ ሦስቱ ዳሬክቶሬቶች ማለትም መደበኛ ወንጀል፣ የኢኮኖሚ ወንጀል እና የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ተግባርና ኃላፊነታቸውም በዋናነት ወንጀል ተፈፅሞ ሲገኝ በወንጀል ተጠርጣሪዎች ላይ የወንጀል ምርመራ፣ ክስና ተከራክሮ ማስቀጣት እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮችን በህግ አግባብ የሚያከናውኑ ሆነው ተደራጅተዋል፡፡
- በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት ደግሞ በክልሉ ፍትህ ቢሮ በወንጀል ዘርፍ ስር የተደራጀ አንዱ የስራ ክፍል ሲሆን ከላይ በተመለከተው ማኑዋል ቁጥር 12.1.4 በተገለፀው መሰረት የሀብት ምርመራ ማድረግ ወይም እንዲደረግ ማዘዝ፣ ተጣርቶ በሚቀርበው የምርመራ ውጤት መሰረት ከላይ የመውረሻ መንገዶች ተብለው በተጠቀሱት መንገዶች በወንጀል እና በፍትሐብሔር ጉዳይ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ አቅርቦ በመከራከር ሀብቱን የማስመለስና ሌሎችንም ተያያዥ ስራዎችን እንዲሰራ ተደርጎ በአዲስ ተደራጅቷል፤
- በአጠቃላይ በማንኛውም የገንዘብ ጥቅም በሚያስገኙ ወንጀሎች በወንጀል ድርጊቱ የተገኘውን ሀብት ለማስመለስ የሚከናወኑ ተግባራትን የመለየት፣ የማጣራት/ምርመራ፣ የማሳገድ/መያዝ፣ ማስተዳደር፣ የማስወረስ እና የመረከብ ስራዎችን እንዲሰራ ተግባርና ኃላፊነቱ ተሰጥቷል፡፡
- ፍትህ ቢሮው በተጨማሪም በክልሉ ተፈፃሚ የሚሆን በወንጀል የተገኘ ንብረት ምርመራና ማስመለስ የአሰራር ማኑዋል አዘጋጅቶና አፅድቅ ከጥር 17 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡

## 8. <u>በወንጀል የተገኘን ንብረት ለማስመለስ ተሳታፊ ወይም ባለድርሻ አካላት</u>

በወንጀል የተገኘን ንብረት ለማስመለስ በአንድ ወገን ብቻ የሚሰራ ሳይሆን በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ከፍተኛ የሆነ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ትብብሮ እና ግንኙነቶች የሚያስፈልገው ነው፡፡

በክልል ደረጃም በወንጀል የተገኘን ንብረት የማስመለስ ስራው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተሳታፊ የሆኑ አካላት የሚከተሉት ናቸው፡

- በአብክመ ፍትህ ቢሮ በወንጀል የተገኘ ሃብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት፣
- የአብክመ ፍትህ ቢሮ እና በስሩ የሚገኙ ሌሎች የስራ ክፍሎች
- የአብክመ ፖሊስ ኮሚሽን
- የፌደራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ቢሮ፣
- ፍትህ ሚኒስቴር
- የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት፣
- የመረጃ ደህንነት አገልግሎት
- የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር አገልግሎት፣
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ፣
- ፍርድ ቤት
- የክልል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ጨምሮ ሌሎች የፍትህ አካላት
- የታገደን ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተረክበው ሊጠብቁና ሊንከባከቡ የሚችሉ የመንግስትና የግል ተቋማት (በፍርድ ቤት የሚሾሙ ንብረት ጠባቂዎች)
- ንብረት የሚፈለግባቸውና የሚታገድባቸው የመንግስትና የግል ተቋማት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 9. ማጠቃለያ

በክልላችን በተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች የመንግስትና የህዝብ ሀብት እየተመዘበረ በወንጀለኞች እየተወሰደ መጠቀሚያ እየሆነ እና ከክልሉ ሊሸሽ የሚችልበት ዕድል ቀላል አይሆንም፡፡ በመሆኑም የተመዘበረውን ንብረት ለማስመለስ ይቻል ዘንድ በክልላችን የአብክመ ፍትህ ቢሮ ቀዳሚ ድርሻውን በመውሰድ ይህን ስራ ሊሰራ የሚችል የስራ ክፍል አደራጅቶ በስራ ላይ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ በወንጀል የተገኘን ንብረት ማስመለስ በአንድ

ተቋም ብቻ የሚታሰብ ሳይሆን የባለድርሻ ተቋማትን ተግባርና ኃላፊነት በሚገባ መወጣትን የሚጠይቅ ነው፡፡ በተመሳሳይ የማህበረሰቡ የነቃ ተሳትፎ የማይተካ ሚና አለው፡፡

ስለሆነም ከክልላችን በወንጀል ምክንያት እየተወሰዱ ያሉ ንብረቶችን ወይም እየደረሰባቸው ያለውን ጉዳት ለመንግስት ለማስመለስ የሁሉም አካል ርብርብ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ የክልሉ ህዝብ በወንጀል ድርጊት በህዝብና በመንግስት ላይ የደረሰ ጉዳት ወይም የተገኘ ጥቅም መኖሩ ሲያውቅ፣ በንብረቱ ላይ የሚኖረውን የባለቤትነት ስሜቱን ተጠቅሞ ጥቆማዎችን በመስጠት እንዲሁም አስፈላጊ ማስረጃዎችን በማቅረብ መተባበር ያስፈልጋል፡፡ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትም በተመሳሳይ ከህዝቡ የሚጠበቅን ተግባራት የማከናወን ኃላፊነት ያለባቸው ከመሆኑ በተጨማሪ በወንጀል የተገኘን ሀብት በማስመለስ ረገድ በባለቤትነት መስራት የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት መወጣት ይኖርብናል፡፡

በሀገራችን ወጥ የሆነ የተጠቃለለ በወንጀል የተገኘ ንብረትን የሚመለከት ህግ ባይኖርም የተመዘበረውን ንብረት እንደተመዘበረበት ወንጀል ባህሪ ማስመለስ የሚቻልበት የተለያዩ ህጎች አሉ፡፡ ሰለሆነም በክልላችን ስራውን ስናከናውን እንደ ጉዳዩ አይነት አግባብነት ያለውን ህግ በመጠቀም ንብረቱን በማስመለስ ሂደት ላይ የበኩላችንን መወጣት አለብን፡፡